*“ እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፥ እልፍ በሉ፥ እልፍ በሉ፥ ከዚያ ውጡ፥ ርኩስን ነገር አትንኩ ከመካከልዋ ውጡ፥ ንጹሐን ሁኑ።”*

*ትንቢተ ኢሳይያስ 52፥11*

# እውነት
# መንፈሳዊ
# ጋዜጣ

በቦስተን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት
በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚቀርብ መንፈሳዊ ጋዜጣ

# በውስጥ ገጾች

## ርዕሰ አንቀጽ
የመኖራችን ምክንያት…

## ሰማዕቱ ካርተር ሱንግ
ስጋዬን እንጂ ነፍሴ አታገኙም። ነፍሴ የሁሉ ጌታ ወደሆነው ወደ እግዚአብሄር ዘንድ ትሄዳለች። ከዚያም በእርጥብ የበሬ ቆዳ ውስጥ አድርገው ሰፉትና ጸሐይ ላይ አስቀመጡት የጸሐዩ ኃይል እየጨመረ ሲሄድ ቆዳው ቀስ በቀስ እየተኮማተረ እየተኮማተረ ሄዶ ጠበቀ።

## የእግዚአብሔር የልቡ ጥማት
የዳዊት ወታደሮች የንጉሳቸውን የልብ ምኞት ለማርካት በነፍሳቸው ተወራርደው በጠላት ወደተከበበችው ቤተልሔም ሄዱ። የጠላትንም ሠራዊት ጥሰው በመግባት ንጉሳቸው ከተመኘው ምንጭ ውሃ ይዘው መጡ። ዳዊትም በእነርሱ እጅግ ደስ ተሰኘ። እግዚአብሔርም ልክ እንደ ስዎች የልብ ጥማት አለው። በዚህ በክፉ ከተያዘው ዓለም ውስጥ ማን ነው ሰዎችን ነጥቆ የሚያመጣልኝ፣ ማነው የጠላት (የዲያቢሎስን) ሠራዊት ሰንጥቆ ገብቶ ወንጌልን የሚያደርስልኝ የሚል።

## መልካሙ እረኛዬ
ከጥፋት ጉዳና እየመለስከኝ
ከፊቴ ቀድመህ እየመራኸኝ
ማምለጫ ጋሻ ሆንክልኝ




## ተመኘሁ
ወደ ስራ ሳታረፍዱ ስትገቡ ያለመታከት ስትሰሩ አለቃችሁን በአክብሮት ስትታዘዙ በእረፍት ሰዓት ለስጋ ብቻ ስትጠነቀቁ ስታበሉና ስታጠጡት ከጓደኞቻቹሁ ጋር ስትደዋወሉ ስትስቁና ስትጫወቱ ለኔ ልታውሉት የምትችሉት ግዜ እግዚአብሔር  ሰጥቷችሁ ሳለ ጊዜ ጠፋ ቢዚ ነን ስትሉ ለምን በሥጋ አልቅና? ለምንስ አልመኝ? እጅግ ተመኘሁ እንጂ!

## ሰው እንደሚያይ እግዚአብሐር አያይም
ዳዊት ብላቴና ነው የቤት የመጨረሻ ልጅ ያውም የበግ እረኛ ደግሞም ምንም ተስፋ ያልተጣለበት።

## በትሬ
ምን አለህ በእጅህ እያለም ጠየቀኝ
እኔስ ካለ በትሬ ሌላም ነገር የለኝ

# ርዕሰ አንቀጽ
# የመኖራችን ምክንያት

መቼም ሰው ነዎትና እግዚአብሔር በምድር ላይ እንዲኖሩ ዕድሜን ሲጨምርልዎት ዕቅድና ዓላማ ይኖርዎታል ብዬ አምናለሁ። ምናልባትም ለመማር፥ ለማግባት፥ ቤት ለመግዛት፥ ሥራ ለመቀየር። ብቻ በመንፈሳዊም ይሁን በሥጋዊ ሕይወትዎ ሊያከናውኑት የሚያስቡት ዕቅድ (ዓላማ) አለዎት። መልካም ነው!

ታዲያ ዛሬ በዕቅድዎ ላይ በምድር ለመኖርዎ ምክንያት የሆነውን በእርስዎ ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ላስታውስዎ ወደድኩ። ይህንን ስል ረስተውታል ማለቴ ግን አይደለም ይልቅ በደንብ በዕቅድና በዓላማ እንዲዘጋጁ ላሳስብዎ ወድጄ እንጂ።

ሁላችንም እንደምናውቀው ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው በአብ ዘንድ ያለውን ዘላለማዊ ዕቅድ ለመፈጸም ነው። ከዚህም የተነሳ የጠፋውን የሰውን ልጅ ለማዳን እስከ መስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ። ክቡር ሕይወቱን መስዋዕት በማድረግ በጨለማው ግዛት ተዘግተው ይኖሩ የነበሩትን ሁሉ በስሙ የሚያምኑትን ከግዞት ነጻ አወጣቸው።

ጌታ ኢየሱስ ይህንን የአባቱን ዓላማ ፈጽሞ ወደ አብ ቀኝ ከማረጉ በፊት የእርሱን ተልዕኮ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። እነርሱም ለነፍሳቸው ሳይሳሱ በብዙ ተጋድሎና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በወንጌል ዓለምን ገለባበጡ። ሩጫውንም በድል ፈጸሙ። ይህ የሆነበት ምክንያት የመኖራቸው ዓላማ ለወንጌል ነበርና።

እንግዲህ በዘመኑ ፍጻሜ ይህንን የክርስቶስን የማዳን ወንጌል እግዚአብሔር አደራውን በእኛ እጅ ላይ ጥሎታል። ዘመኑ አጭር ነው የጌታም ምጽዓት በደጅ ነውና በጨለማው ስልጣን ስር ያሉ እጅግ ብዙ ናቸውና የሕይወት ውሃ ምንጭ የሆነውን ኢየሱስን በማወቅ ከዘላለም ሞት ያመልጡ ዘንድ የተገለጠልንን የወንጌልን እውነት እንንገራቸው።

የመኖራችን ምክንያት ለሚጠፉት መዳን ለመሆን ነውና! አባቶቻችንን የረዳ የእግዚአብሔር መንፈስ ዛሬም ከእኛ ጋር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም እስከ ለዘላለምም ያው ነው። እስከ ዓለም ፍጻሜ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ያለው ኢየሱስ በቃሉ የታመነ ነው!

በፓስተር ምሕረቱ ለጂቦ



# ሰማዕቱ ካርተር ሱንግ

**የተርጓሚው መልዕክት ይህንን እውነተኛ ታሪክ ሳነብ ውስጤን በጣም ነካኝ ለካ በየዘመኑ ስለ ክርስቶስ ወንጌል ህይወታቸውን ሳይቀር መስዋዕት የሚያደርጉ ብዙ የእምነት ጀግኖች አሉ አልኩኝ ታዲያ አንድ ሀሳብ ወደ ውስጤ መጣ በተቻለ መጠን ወደ አማርኛ ብተረጉመውና ወገኖቼ ቢያነቡት ለሁሉም ጥሩ ነገር ለልባቸው ይቀርላቸዋል በዬ አሰብኩ ከዚህም የተነሳ ወደ አማርኛ መልሼ በዚህ መልኩ ለነባብ አብቅቼዋለሁ**

A.J Apasame በኤ.ጄ አፕሳሚ ከተዘጋጀው The happiness of secret ወይም የደስታ ምስጢር ከሚለው መጽሃፍ አንድ ክፍል የተወሰደ

*ትርጉም በእንግዳአየሁ ጥላሁን*

ካርተር ሱንግ 18ኛው እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መካከል በህንድ ሰሜናዊ ግዛት ይኖር የነበረ ወጣት ሲሆን ከሂንዱይዝምና ከእስልምና ተወጣጥቶ በተፈጠረ (ሲክ) የሚባል ኀይማኖት ተከታይ ነበር። እናቱም በኃይማኖቱ ጠንካራ እንዲሆን ከልጅነቱ ጀምሮ ስትኮተኩት ያሳደገችው ስትሆን ምኞቷ ደግሞ (ሳዱ) እንዲሆንላት ነበር። ሳዱ ማለት በክርስትናው እምነት ባህታዊ እንደሚባለው አይነት ነው ይህ ወጣት እጂግ የታወቀ ፓትሊያክ ሲንግ ሱንዳር አርማና የተባለ በዘመኑ እጅግ ባለጠጋ እና በሃገሩ የተከበረ ሰው ልጅ ነበር ።ካርተር ሱንግ ቅዱሳን መጽሐፍቶችን የማንበብ ለምድ የነበረው ወጣት ሲሆን እውነትን አጥብቆ የሚሻ ልብ ነበረው። በአንድ ወቅት መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ የክርስቶስ አዳኝነት በራለት ታዲይ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስን መከተል ጀመረ በዚህ ምክንያት ነበረ ከፍተኛ ስደትና ጥላቻ የደረሰበት አባቱ የጀመረውን የክርስትና እምነት በአስቸኳይ እንዲያቆም ማስጠንቀቂያ አዘል ትዕዛዝ ሰጠው በመቀጠል የተለያዩ እርምጃዎችን ወሰደ በዚህ ሁሉ ግን ምንም ለውጥ አላገኘም በመጨረሻ ልጁ ለአባቱ እንዲህ አለው አባቴ ሆይ ስማኝ ለብዙ ጊዜ የውስጥ ሰላም የሚሰጠኝ ፍለጋ በብዙ መንገድ ደከምኩ ግን ምንም አላገኘሁም ብዙ የኃይማኖት መጻፍቶችን አነበብኩ ፤ጾምኩ፤ ጸለይኩ፤ ሰገድኩ ምንም ሰላም ግን ማግኘት አልቻልኩም አሁን ግን እግዚአብሔር በቃሉ ዕውነትን አበራልኝ ስለ እኔ ሕይወቱን መስዋዕት አድርጎ ያዳነኝን ክርስቶስን አገኘውት አሁን እውንተኛ የውስጥ ሰላም አለኝ ከዚህ እውነት ማንም ሊነቀንቀኝ አይችልም አለው ። በመጨረሻም አባቱ በጣም የሚወዳትን የልጁን እጮኛ አስጠርቶ የሆነውን ሁሉ አስረዳት ልተመልሰው የምትችል ከሆን የተቻላትን ሁሉ እንድታደርግ ነገራት ልጅቱ በንግዋር ክንዋራ የምትባል ስትሆን ውብና ጨዋ በባህልዋም እጅግ የተከበረች ነበረች ካርተር ሱንግንም በማግኘት እንዲህ አለችው አንተ እድለኛ ብዙ ተስፋ ያለህ ሰው ነህ በምቾት ትኖራለህ ከአባትህም ባለጠግነት የተነሳ ብዙ ክብር የሚጠብቅህ ወጣት ነህ ስለዚህ አሁን የጀመርከው ጎዳን የሚያዛልቅህ አይደለም በደንብ ብታስብበት ጥሩ ይመስለኛል ።አልያ በስተመጨረሻ በወሰድከው የተሳሳተ እርምጃ እጅግ ይጸጽትሃል አለችው።እርሱም እንዲህ አላት እባክሽን ማሰናከያ አትሁኝ አሁን ክብር ብለሽ ያወራሻቸው በሙሉ እንደሳር ጠውልገው ያልፋሉ ነገር ግን ክርስቶስ ለኔ የማያፍ የዘላለም ህይወት እና የልጅነት ስልጣን ሰጥቶኛል አንቺም ለዚህ ጌታ ልብሽን በመስጠት የዚህ እድል ተካፋይ ብትሆኚ መልካም ነው አላት። እርሷ ግን ገና ድሮ ነው ለአንተ ልቤን የሰጠውህ አንተም ዛሬ ልብህን ለኔ ስጠኝ አለችው ውድ ደንግዋር እኔ ያለኝ አንድ ልብ ብቻ ነው እርሱንም ለክስቶስ ሰጥቼዋለሁ ለአንቺ የምሰጥሽ ሌላ ልብ የለኝም ከየትም ላመጣ አልችልም አንቺም ብትሆኝ ልብሽን ከኔ ወስደሽ ለክርስቶስ ስጪው አላት በዚህን ጊዜ ነበር ተስፋ በመቁረጥ ምርር ብላ ያለቀሰችው ሁኔታውንም ለአባቱ በሃዘን ነገረችው አባቱም ካርተር ሱንግን በቁጣ አስጠርቶ የለበሰውን ልብስ እንዲያወልቅ አዘዘው እንዲህም አለው ከዚህ በኋላ ልጄ አይደለህም ከኔ ጋር ያለህን ግንኙነት ሁሉ በገዛ ፍቃድህ አሁኑኑ አቋርጠሃል ብሎ ከሞቀና ካደገበት ቤቱ ውጣ አለው ልጁም ልብሱን አውልቆ በአባቱ እግር ስር አኖረው አባቱንም ዛሬ ይህንን ልብስ በማውለቄ አላፍርም ምክንያቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ እራቁትነቴንና ሐጢያቴን ሸፍኖልኛል ይህንን ካለ ቦኋላ እየጸለየ ቤቱን ለቆ ወጣ ለተወሰኑ ቀናት በጫካ ውስጥ ቆየ በረሃብና በብርድ ቢሰቃይም ልቡ ግን በሰላም የተሞላ ነበር በተደላደለ ቤት ውስጥ በምቾት ላደገ ወጣት ይህ ሁኔታ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው

ይህ ወጣት ችግር፤ድህነት፤ረሀብ በፍጹም አያውቅም አሁን ግን ስለ ወንጌል ተቸገረ ፤ተራብ ከሞቀና ከሞላ ቤቱ ወጥቶ ማደሪያ መጠለያ የሌለው ምስኪን ሆነ ስለዚህ ኑሮውን ለማሸነፍ የግድ ማድረግ የነበረበት ወደ አንድ አካባቢ ሄዶ ስራ ለመስራት መሞከር ብቻ ነው እናም የጉልበት ስራ ሊሰራ እንደሚፈልግ አንድ ግለሰብ በማነጋገር ከእርሱ ጋራ መስራት ጀመረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሰራውን አጠራቅሞ የተለመደውን የሃገሩን ባህል የሆነውን ረጅም ልብስና ጥምጥም ለመግዛት ቻለ በእርግጥ ቀድሞ በአባቱ ቤት የነበረው የክብር ልብስ ባይሆንም እርሱ ደስተኛ ነበር ከዚህ በኋላ ነበር ወንጌልን አነግቦ የተሰቀለውን የክርስቶስን አዳኝነት ለመስበክ በሃገሩ ውስጥ ካሉት ቲቤት ወደሚባል ግዛት የሄደው የቲቤት ከተማ በሆነችው በካሺንጋ ወንጌልን በኃይል በየቦታው መስበክ ጀመረ ከዚህም የተነሳ የከተማው ነዋሪዎች እንግዳ ነገር እንዳመጣባቸው አስበው ክፉኛ ጠሉት ያም ኒሆን ለተወሰኑ ዓመታት ወንጌልን በብዙ ችግር ማሰራጨት ችሎ ነበር ሆኖም ህዝቡ በእርሱ ላይ ከነበራቸው ጥላቻ የተነሳብ ብዙ መልኩም ከከተማቸው እንዲወጣ ሞከሩ ነገር ግን በገዛ ራሱ እንደማይሄድ ስለተረዱ በጨርቅ ጠቅልለው አሰሩትና የሚበቃቸውን ያህል ከደበደቡት በኋላ ከንግዲህ ሰው አይሆንም ብለው ስላሰቡ ከክልላቸው አውጥተው ጣሉት እርሱ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በፍጹም ባልጠበቁት ሁኔታ ተመልሶ መጣ ይህንን ባዩ ግዜ ከሰው ለፍርድ አቀረቡት ግዛቱን በሚያስተዳድረውና በዳኛው በአበሞኔት የሞት ፍርድ ተፈረደበት ካርተር ሱንግ ይህንን ሲሰማ እንዲህ አለ የፈለጋችሁትን ልታደርጉ ትችላላችሁ እኔ ግን የኢየሱስን አዳኝነት እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ መናገሬን አልተውም ምክንያቱም ለእኔና ለእናንተ ያለውን ፍቅር ሕይወቱን በመስቀል ላይ መስዋዕት እስኪያደርግ ድረስ ተገልጿል እኔም ከርሱ ፍቅር የተነሳ እናንተ በርሱ አምናችሁ ከጥፋት እንድታመልጡ ህይወቴን እንኳን ሳይቀር መስዋዕት ላደርግ ተዘጋጅቻለሁ አሁንም የምነግራችሁ ነገር ቢኖር ንሰሃ ግቡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመኑ ያለ በለዚያ የዘላለም ሞት ፍርድ ይጠብቃችኋል አላቸው ከዚያም ወደ ፍርዱ ወደ ሚፈጸምበት ቦታ ወሰዱት እንዲህ አለ አሁን በዚህ ቦታ ፍርዳችሁ ሊከናወን ነው ነገር ግን ስጋዬን እንጂ ነፍሴን

አታገኙም ነፍሴ የሁሉ ጌታ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሄር ዘንድ ትሄዳለች ከዚያም በእርጥብ የበሬ ቆዳ ውስጥ አድርገው ሰፉትና ጸሐይ ላይ አስቀመጡት የጸሐዩ ኃይል እየጨመረ ሲሄድ ቆዳው ቀስ በቀስ እየተኮማተረ እየተኮማተረ ሄዶ ጠበቀ ያ ታማኝ አገልጋይ ይህን በመሰለ ስቃይ ውስጥ ሆኖ የምስጋና መዝሙሮችን እየዘመረ እና ስለ ጠሉት ሰዎች ደህንነት እየጸለየ ቆየ ሰዎቹም ይህንን በመሰለ አሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በጣም ሲደሰትና አምላኩን ሲያመሰግን በማየታቸው ተገርመው አንዳዶቹ ምናልባት በማይታወቅ መንፈስ ተይዞ ይሆናል አሉ በዚህ ሁኔታ አራት ቀን ሙሉ ሲያሰቃዩት ከቆዩ በኋላ ከስቃይ ነጻ የሚሆንበት ወደ ዘላለም እረፍት የሚገባበት ጊዜ እንደደረሰ በመንፈሱ ተረዳ አንድ እጁን እንዲያወጡለትና ጥቂት የመጨረሻ ቃላት ብቻ ለመጻፍ ፍቃድ ጠየቀ በዚህ መሰረት አንድ እጁ ከወጣ በኋላ በዳኛው እጅ ይገኝ በነበረው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ገጾች በአንዱ ላይ የሚከተለውን ጻፈ ኢየሱስ ሕይወቱን ሰጠኝ የሰጠኝ ሕይወት የእርሱ ነው እውነቱ ግን በምንም ዓይነት መንገድ ውለታውን አለመመለሴ ነው ሙሉ ዋጋ ልከፍል የምችለው ለዚ ለውድ ስም ክብር ራሴን ሺህ ጊዜ የሰዋሁ እንደሆን ብቻ ነው እግዚአብሄር አንድ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ስለ ወንጌል መቶ ሺህ ጊዜ ለመሞት እንድችል መቶ ሺህ ሕይወት ቢሰጠኝ ጥሩ ነበር ለርሱ ያለኝ ፍቅር ከባሏ አስከሬን ጋር ከምተቃጠል ከሂንዱ ሴት ፍቅር እንዳያንስብኝ ነው ጸሎቴ እርሷ ዳግመኛ ልታገኘው ተስፋ ለማታደርገው ለሞተ ብሏይህንን ያህል ካደረገች እኔ ስለ ሕይወቴ አዳኝ ያውም ስለኔ ሞቶ ሞቴን ለሻረልኝ ውድ አምላኬ ምን ያህል የበለጠ ማድረግ ይገባኛል የሂንዱ ሴት ለባሏ ከምታደርገው ያነሰ ነገር ማድረግ ለኔ የሚያሳፍር ነው ከዚያ ለተሰበሰቡት ሰዎች የቆማችሁት የክርስቲያንን ሞት ለማየት ነውን  ጠጋ በሉና እዚህ የሚሞተው ክርስቲያን ሳይሆን ሞት ራሱ እንደሆን ተመልከቱ ካላቸው ቦኋላ ጌታ ሆይ የአንተ ናትና ነፍሴን በእጅህ  አደራ እሰጣለሁ ተቀበለኝ በማለት ከጌታው ጋር በዘላለም እረፍት ለመኖር ሄደ ።

# የእግዚአብሔር የልቡ ጥማት

መቼስ ሰው ሁሉ የልብ ጥማት አለው ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ታዲያ ያንን የልቡን ጥማት ለማግኘት ብዙ ዋጋ በመክፈል ይታገላል። አንዳንዱ የሕይወት ወስዋዕትነት የሚጠይቅ ይሆንና ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ የሆነ ትግል ውስጥ ይገባል። ድንገትም የተመኙትን ለማግኘት በሚደረግ ትግል ውስጥ የብዙዎች ሕይወት ያልፋል አንዳንዱም በድል ያጠናቅቃል።ያም እንኳን ሆኖ የሰው ልጅ የልቡን ጥማት ለማግኘት የሚያደርገው ትግል በሕይወቱ ላይ የማይሻር ጠባሳ ጥሎበት ሊያልፍ ይችላል።

ታዲያ ንጉሥ ዳዊት በአንድ ወቅት በጠላት ከተከበበችው የቤተ-ልሔም የውሃ ምንጭ እጅግ ውሃ ተጠማ። በዙሪያው ብዙ ውሃ አለ ነገር ግን የነፍስ ዋጋ በሚያስከፍል ሁኔታ ውስጥ ካለችው የቤተልሔም የውሃ ምንጭ ውሃ ተመኘ። 2ኛ ሳሙኤል 23፥13 — 16 እንዲህ ይላል፦ "ከሰላሳውም አለቆች ሶስቱ ወርደው በመከር ጊዜ ወደ ዳዊት ወደ ዓዱላም ዋሻ መጡ የፍልስጥኤማውያንም ጭፍራ በራፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ነበር።  በዚያ ጊዜ ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ።  የፍልስጥ ኤማውያንም ጭፍራ በዚያ ጊዜ በቤተልሔም ነበር።  ዳዊትም በበሩ አጠገብ ካለችው ከቤተልሔም ምንጭ ውሃ ማን ባጠጣኝ ብሎ ተመኘ። ሶስቱም ኃያላን የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ቀድደው ሄዱ።  በበሩም አጠገብ ካለችው ከቤተልሔም ምንጭ ውሃ ቀዱ ይዘውም ለዳዊት አመጡለት" ይላል።

እነዚህ የዳዊት ወታደሮች የንጉሳቸውን የልብ ምኞት ለማርካት በነፍሳቸው ተወራርደው በጠላት ወደ ተከበበችው ቤተልሔም ሄዱ። የጠላትንም ሠራዊት ጥሰው በመግባት ንጉሳቸው ከተመኘው የውሃ ምንጭ ውሃ ይዘው መጡ ዳዊትም በእነርሱ እጅግ ደስ ተሰኘ።

ወገኖቼ፣ እግዚአብሔርም ልክ እንደ ሰዎች የልብ ጥማት አለው።  ጳውሎስ በመልዕክቱ  ዓለም ሁሉ በክፉ እንደተያዘ እናውቃለን ይላል።ታዲያ እግዚአብሔር በዚህ በክፉ ከተያዘው ዓለም ውስጥ ማን ነው ሰዎችን ነጥቆ የሚያመጣልኝ፣ ማነው የጠላት (የዲያቢሎስን) ሠራዊት ሰንጥቆ ገብቶ ወንጌልን የሚያደርስልኝ የሚል የልብ ጥማት አለው።  ለወንጌል ሥራ ልባቸው የቆረጠ፣ የጨከነ ሰዎችን ይፈልጋል።  እነዚያ የዳዊት ወታደሮች ለነፍሳቸው ግድ አልነበራቸውም።  ራዕያቸው አንድ ነበር - የንጉሣቸውን የልብ ጥማት ማርካት።  ስለዚህ ወገኖቼ የንጉሳችን የልብ ጥማት ዓለምን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ መጠቅለል ነው። ለዚህ ደግሞ የተመረጠ ሠራዊት እኛ ነን።  ኤፌሶን 2፥10 ላይ "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" ይላል።  ለዚህ ለወንጌል ስራ ሁላችንን ጌታ እንደመረጠን ይህ ክፍል በግልጽ ይናገራል።

ምክንያቱም መልካሙን ስራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን ነው የሚለው። ለምን እንደተፈጠርን በግል ይናገራል። እንደገና ሁላችንንም እንደሚፈልገን ያሳያል። ስለዚህ ማወቅ ያለብን ትልቁ ቁምነገር ቢኖር እግዚአብሔር በምድር ላይ እንድንኖር እድሜን የሚጨምርልን አላማው አንድና አንድ ብቻ መሆኑን ነው። እርሱም ለወንጌል ስራ ሌላው ሁሉ ሁለተኛ ወይንም ያእግረ መንገድ ጉዳይ ነው። ብዙዎቻችን ግን በዋናው ሳይሆን ለምድርና በምድር በሚቀረው ጊዜአዊ ነገር ተጠምደን ቆመናል። ከዚህ በኋላ ግን ልባችንን እናጠንክር፣ ከጌታ ጋር እንስማማ።  ንጉሣችንን ልዑል እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ጨክነንና ቆርጠን እንነሳ።

ወንጌል የቅብብሎሽ ሩጫ ነው።  የቀደሙት አባቶቻችን ስለ ወንጌል የነፍስ ዋጋ ከፍለው እዚህ አድርሰውልናል።  ይህ የወንጌል አደራ ዛሬ በእኛ ላይ ወድቋል።  የዘመኑ ተረኛ ወታደሮች በልዑል እግዚአብሔር ፊት የምንቆም እኛ ነን።  ነገር ግን ዛሬ ላይ ቆመን ሁሉን ስናይ በብዙ በማይረቡና ጌታን ደስ በማያሰኙ ነገሮች ተይዘናል።  ብዙዎቻችን የንጉሣችንን የልብ ጥማት እያየን እንደ ዳዊት ወታደሮች ዋጋ ከፍለን ከማገልገል ይልቅ በራሳችን አጀንዳ ተይዘን ቆመናል።

ዛሬ ግን ይብቃን ከታነቅንበት ምድራዊ አጀንዳ እንውጣ ልዑል እግዚአብሔር ይጠብቀናል።  የተጫነንን የኃጢአት፣ የቸልተኝነት የድካም ሕይወትን አራግፈን የእግዚአብሔርን የልብ መሻት ለመፈጸም እንነሳ።

*በሔኖክ ተሾመ*

# ተመኘሁ

በስጋ ላይ እጅግ እየተመኘች
ከውስጥ ከልብ ሆና ትጮሀለች
ጆሮ ያለው ይስማ እያለች
መንፈስ ድምጽ አውጥታ ትጣራለች

የእግዚአብሔር ቃል በገላትያ 5፤17 “ስጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ይመኛልና እነዚህ እርስ በእርሳቸው ይቀዋወማሉ” እንደሚል እኔ መንፈስ በስጋ ላይ እጅግ ተመኘሁ፥ ቀናሁ ተቃወምኩ። ታዲያ ምን ያደርጋል እናንተ ለስጋ አድልታችሁ ምኞቴንና ተቃውሞዬን ሁሉ ከንቱ መና አደረጋችሁብኝ?

ምን አድርገን ለስጋ አደላን ምኞትሽንስ መቼ ከለከልን የምትሉ ከሆነ ስለ እውነት እንፋረድ እንዋቀስ ጩኸቴን፥ መጣራቴን፥ ቅናቴንና ጉጉቴን ሰምቶ እንዳልሰማ ሆናችኋል?

በማለዳ ትነሱና እኔ ትዝም ሳልላችሁ በመታጠብ፥ በመኳኳል፥ ለወቅቱ የሚመች ልብስ በመልበስ የጣፈጠ ምግብ በመብላት እኔ ግን ተርቤ ብታዩም ዝም በማለት ወደ የሥራ በፍጥነት ትወጣላችሁ። ታዲያ ይሄ ሁሉ ለሥጋ ሲደረግ ምነው ለኔ ቢሆን ብዬ በስጋ ላይ ተመኘሁ።

ወደ ሥራ ሳታረፍዱ ስትገቡ ያለመታከት ስትሰሩ አለቃችሁን በአክብሮት ስትታዘዙ በእረፍት ሰዓት ለስጋ ብቻ ስትጠነቀቁ ስታበሉና ስታጠጡት ከጓደኞቻቹሁ ጋር ስትደዋወሉ ስትስቁና ስትጫወቱ ለኔ ልታውሉት የምትችሉት ጊዜ እግዚአብሔር ሰጥቷችሁ ጊዜ ጠፋ ቢዚ ነን ስትሉ ለምን በስጋ አልቀና ለምንስ አልመኝ እጅግ ተመኘሁ እንጂ!

ትምህርት ቤት ገብታችሁ ያለ ድካምና መሰልቸት ለሰዓታት ስታነቡ ንቁ በመሆን ፈተና ለማለፍ ስታጠኑና አስተማሪ የሚሰጠውን ገለጻ በትጋት ስትከታተሉ ነገር ግን ቤተ-ክርስቲያን መጥታችሁ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገባ መከታተል ሲገባችሁ ስትታክቱ፣ ለደቂቃ ቃሉን አንብባችሁ ዓይናችሁ በእንቅልፍ ሲያዝ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ላለመገኘት ሰበብ ስታበዙና ስትቀሩ በስጋ ላይ እኔ መንፈስ በጣም በቅናት ተመኘሁ።

ከሥራ በኋላ ቤት በመግባት ቲቪ፥ ሙቪ፥ ጌም ስታዩ ስትዝናኑ ትቆዩና ራታ በልታችሁ የእኔን ነገር ችላ በማለት ስጋችሁን ልታሳርፉት ወደ መኝታ ስታመሩና ሞቋችሁ ስትተኙ እኔ ግን ሲበርደኝ እንዴት በስጋ ላይ አልቀና?

አንዳንዶቻችሁ በሳምንት አንድ ቀን ለዚያውም በማርፈድ ሁለት ሰዓት ለማትሞላ ጊዜ ቤተ-ክርስቲያን እየመጣችሁ ስድስቱን ቀን ግን ለስጋ በሚሆን ነገር ተጠምዳችሁ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የምትደፍኑት ስንት ቀዳዳ እያለ ሌሎች ወንድምና እህቶች አገልግሎት ተደራርቦባቸው እያያችሁ ዞር በማለት ጀርባችሁን ስትሰጡ እግዚአብሐር የሰጣችሁን ጸጋ በማዳፈን ስትወጡ ሳይ በስጋ ላይ በምኞት ተቃጠልኩ!

እኔ መንፈስ ሳልጐዳ የተመኘሁ በስጋ ላይ እንዲያው የቀናው ይመስላችኋል? እነሆ ያዕቆብ 4፤5 “በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅናት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደተናገረ ይመስላችኋልን?” እስቲ ስሙኝ! መማር፥ በትጋት መስራት፥ መብላትና መጠጣት እንዲሁም የሚያስፈልጋችሁ ማድረጋችሁ መልካም ሆኖ ሳለ ነገር ግን ከእኔ ጋር ያላችሁን ሕብረት ካስጣለ፥ ካስረሳ ስጋችሁ በእናንተ ላይ መንገሱም አይደል?

በሮሜ 8፥6 “ስለ ስጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው ስለ ስጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና” የሚለው የእውነት ቃል ምነው ለዘላለም በገባቸው ብዬም ተመኘሁ።

ትዝ ይላችኋል ያኔ ገና በማለዳ ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኝ በማድረግ ስትቀበሉ አቤት ፍቅር፤ ከኔ ጋር የነበራችሁ ሕብረት፤ መጣበቃችሁ ከእናት ከአባት ከወዳጅ ከዘመድ ይልቅ የኔን ምክር ስትሰሙ ስትታዘዙ አስታውሳለሁ ለስጋችሁ ብዙም ግድ አልነበራችሁም። ጊዜ፥ ዕውቀት፥ፈቃድ፣ስሜታችሁን፥ዓላማ፥ዕቅድ፥ሥራ፥መንገዳችን ሁሉ ከኔ በኋላ ነበር ያደረጋችኋቸው አቤት ያኔማ! በእግዚአብሔር ቃል ፤ በምስጋና ፤ በጸሎት ፤ በዝማሬ ፤በግላችሁና በሕብረት ሁሉ ሁሌ የኔን ምሪት ነበር የምትቀበሉት የምታደርጉትን ሁሉ በእውነትና በመንፈስ ነበር የምታደርጉት……ዋ ያኔማ! ስጋችሁ በእኔ ይቀና ነበር እናንተም አብልጣችሁ በጾምና በጸሎት እኔን አጠንክራችሁ ሥጋችሁን ትበድሉት ነበር!

ታዲያ ዛሬ ምነው ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆነ? ያን ፍቅራችሁን ከኔ ጋር የነበራችሁን ሕብረት የት አደረሳችሁት ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል እንዲሉ አፈር የሆነው ስጋችሁ ለኔ የነበራችሁን ፍቅር ጠራርጎ ወሰደው። በእኔና በእናንተ መካከል ጣልቃ በመግባት ምኞትና ቅናት ውስጥ ከቶኛልና መጽሐፉ እንዲል የምነቅፍባችሁ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅራችሁን ትታችኋልና ራዕይ 2፥4 ስለዚህ ጊዜው አሁን ነው ሳትዘገዩ የቀደመውንና ያስለመዳችሁኝን ፍቅራችሁን ስጡኝ ወደ ቀድሞ ቦታዬ ልመለስ ያንን አጉል ልምድ በማስለመድ በማቀማጠል የማይገባውን ቦታ የሰጣችሁትን ሥጋ ጎስሙት ስቀሉት የእግዚአብሔርን ቃል “እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም” ይላልና በተሰጣችሁ የፍቅር መንፈስ እኔን መንፈስን ውደዱ ሥጋንና ምኞቱን ጥሉ ባላችሁ የኃይል መንፈስ የስጋን ምኞት ሁሉ አሸንፉ በተቀበላችሁት ራስን የመግዛት መንፈስ ራሳችሁን ገዝታችሁ የመንፈስን ነገር ብቻ አድርጉ። እሺ ብትሉ ብትታዘዙ በሙሉ ልብ ለማድረግ ብትነሱ ትችላላችሁ በገላትያ 3፥3 በመንፈስ ጀምራችሁ በስጋ ትጨርሳላችሁን የሚለው ቃል በእናንተ አይድረስ ብዬ ተመኝቼ አበቃሁ።

*በሐብታሙ አስረስ (ሐብቴ)*

# ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም

ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራና ጻድቅ ሰው ነበር። ከዚህም የተነሳ አንድ ቀን እግዚአብሔር በእርሱ ተወራረደ። በዚህም ምክንያት አስደንጋጭ እና ተደራራቢ አደጋ ድንገት ደረሰበት። ይህንን ያዩ ሰዎች ሐጢያተኛ ነህ ለኃጢአትህ ደግሞ ልክ የለውም አሉት። በጓዳ እና በአደባባይ የሰሞኑ የወሬ አጀንዳቸው እርሱ ሆነ። ንስሐ ብትገባ ይሻልሃል፣ ይህ በአንተ ላይ የደረሰው መቅሰፍት በትክክል የኃጢአት ውጤት ነው እንዲህ ያለ መከራ በከንቱ ሊደርስብህ አይችልም፣ እግዚአብሔር ተቆጥቶህ ነው አንተ ግን ራስህን ጻድቅ ታደርጋለህ። ይህ እግዚአብሔርን የመዳፈር ያህል ነው አሉት። ኢዮብም በየቀኑ ህመሙ እየባሰበት ሄደ ሰውነቱም በጣም ከመቁሰሉ የተነሳ በገል ማከክ ጀመረ ከዚህም የተነሳ ሰው ሁሉ በእርግጥ ይህ ሰው ኃሐጢአተኛ ነው ብለው ደመደሙ። አይ ሰው! ኢዮብ 22፥1-12



ሐና ልጅ ባለመውለዷ ምክንያት እጅግ በሐዘን የተመታች መካንነቷ ለስድብ የዳረጋት የውስጥ ችግሯን የሚያውቅላት ያጣች የነፍሷ የጣር ጩኸት ሊገባው በሚችል በእግዚአብሔር ፊት ድምጿን ሳታወጣ ስትጸልይ ያያት ካህኑ ዔሊ የከንፈሯን እንቅስቃሴ ብቻ አይቶ አንቺ ሴት ስካርሽ እስከመቼ ነው የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው አላት። አይ ሰው! ምን ያድርግ? የልብ ማየት አይቻልማ የሚገርመው ነገር ታዲያ የውስጥ ጩኸት የሚሰማ ጌታ መካኒቷን በልጅ ደስ አሰኛት። ሃሌ ሉያ! ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይማ። 1 ሳሙኤል 1፥1-20

ጌዴዎን የፈራና የደነገጠ በወይን መጥመቂያ ጉድጓድ ውስጥ እህል የሚወቃ ከሚዲያማውያን አስጨናቂ አገዛዝ የተነሳ በጥያቄ የተሞላ ለራሱም ሆነ ለወገኖቹ ያለው ግምት ዝቅተኛ የሆነ ወገኑ ከምናሴ ነገድ ከሁሉ ይልቅ የተጠቃ ነው። እኔም በአባቴ ቤት የሁሉ ታናሽ ነኝ የሚል እራሱን ምንም ተስፋ እንደሌለው አድርጎ የሚቆጥር። አይ ሰው! ደስ የሚለው ታዲያ እግዚአብሔር መጣና አንተ ጽኑ ሃያል ሰው አለው። ሃሌ ሉያ! ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይማ! መሳፍንት 6፥11-12

አመንዝራይቱ ሴት ሰዎች ሁሉ በኃሐጢአቷ ምክንያት ሊወግሯት የቻሉትን ያህል ድንጋይ ይዘው እያዳፏት በጌታ ፊት አመጧት። ግማሹ ይጮሃል፣ ግማሹ ያፏጫል፣ ሁሉም በየፊናው የተሰማውን እየተናገረ ይፈርድባታል። ሙሴ የሰጠን ሕግ እንደሆነ "ሲያመነዝር የተገኘ በድንጋይ ተወግሮ መሞት አለበት።" እያሉ ወደ ጌታ ፊት አመጧት። ሁሉም አንድ ቃል ይጠብቃሉ "ውገሯት!" የሚል። አይ ሰው! የሚገርመው ነገር ታዲያ ጌታ ግን በነጻ አሰናበታት እንዲህ ብሎ፦ "ልጄ ሆይ ደግመሽ ኃጢአትን አትስሪ።" ሃሌ ሉያ! ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይማ!

ዳዊት ብላቴና ነው። የቤት የመጨረሻ ልጅ ያውም የበግ እረኛ ደግሞም ምንም ተስፋ ያልተጣለበት። ለንጉስነት ሰው ቢፈለግ አባቱ ታላላቆችን አቅርቦ እርሱን ግን የረሳው በፍጹም ግምት ውስጥ ያልገባ፣ ሌላ ልጅ የለህም ተብሎ ቢጠየቅ እንኳን እየተጠራጠረ "አለኝ ግን የሁሉ ታናሽ ነው ደግሞ እዚህ የለም በምድረ በዳ በግ እየጠበቀ ነው ያለው።" ተጠርቶ በመጣ ጊዜ እንኳን ነብዩ አይቶት በፍጹም እርሱ ሊሆን ይችላል ብሎ ያልገመተው። አይ ሰው! በጣም የሚገርመው ነገር ታዲያ እግዚአብሔር ለነቢዩ እንዲህ አለው፦ "ሰው ውጭን ያያል እኔ ግን ልብን አያለሁ።" ስለዚህ የመረጥኩት እርሱ ነውና ተነስተህ ቀባው አለው። ሃሌ ሉያ! ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይማ! 1ኛ ሳሙኤል 16፥6-13



ወንድሜ ዛሬስ አንተ በምን ሁኔታ ውስጥ እያለፍክ ይሆን? እህቴስ? ሰዎች ስለ አንቺ ምን ዓይነት አመለካከት ይኖራቸው ይሆን? ምንስ እያሉ ነው? እንደ ኢዮብ በመከራ ስለተከበብህ እና ለበሽታህ ፈውስ ስላልመጣ እንደ ኃጢአተኛ ተቆጥረትህ ይሆን? እንደ ጌዴዎንስ ነገር ሁሉ ግራ አጋብቶህ ፈሪ ሆነሃል? ወይንስ ራስህን ምንም ተስፋ እንደሌለህ አስበህ - ምነው ጌታ ዛሬ በወሰደኝ ብለህ ይሆን? እንደ ዳዊትስ ታናሽነትህን አይተው ንቀውሃል? እህቴስ እንደ ሐና መካንነትሽ ለስድብ ዳርጎሻል? እግዚአብሔር ማህጸንሽን እስኪከፍት ድረስ ጸንተሽ በጠበቅሽ እንደተረገምሽና በእግዚአብሔር እንደተቀሰፍሽ ቆጥረውሽ ይሆን? ወይንስ አንድ ቀን አቅም አጥተሽ በኃጢአት ብትወድቂ ሁሉም ሊወግሩሽ ድንጋይ አንስተውብሻል?

ወገኖቼ ዛሬ ግን አንድ የሚያጽናና እና የሚደገፍ እውነት እንደ እግዚአብሔር ቃል ልንገራችሁ። "ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም።" ትንሽ ብትሆን የማይንቅህ፣ አፍሽን ሳትከፍቺ ብትጸልይ የውስጥ ልመናሽ የሚገባው፣ ከደረሰብህ ከባድ ሁኔታዎች የተነሳ በፍርሃትና በድንጋጤ ተውጠህ ቢሆን የወደፊቱን አይቶ አንተ ጽኑ ኃያል ሰው የሚልህ፥ በኃሐጢአት ብትወድቂ በምሕረት የሚቀበልሽ፥ በበሽታ እየማቀቅህ ቢሆን ፈውስን ሰጥቶ ለክብሩ በአደባባይ ሊያቆምህ የተነሳብህን ማዕበልና ወጀብ ሁሉ ጸጥ በል ሊለው - ያጎበጠህን ቀንበር ሊሰብር፥ የፈረዱብህን በሥራቸው ተጸጽተው ወደ ኋላ ሲሉ ልዑል እግዚአብሔር በግርማ ሞገሱ ወደ አንተ፣ ወደ አንቺ ፈጥኖ ይመጣል። አሜን!

*በወንድም ሄኖክ ተሾመ*

## በትሬ

በንጉሥ ቤት ነበር የኔ አስተዳደጌ
ጥበብን ዕውቀትን መማር ወግ እና ማዕረጌ
ነገር ግን በአንድ ወቅት ደጃፌ ተከፍቶ
አይኔን ቀና ሳደርግ ሳልጠብቀው ከቶ
ወገኔ ሲበደል አይኔ ተመልክቶ
ገብጻዊውን ገደልኩት ውስጤ ተቆጥቶ
ታዲያ በዚህ ምክንያት ስደት ደረሰብኝ
ከግብጽ ሸሽቼ ዩተር ቤት ገባሁኝ
በግ ጠብቄ አላውቅም ልምዱም አልነበረኝ
ነገር ግን ላማርጥ ዕድል ስለሌለኝ
በበግ እረኝነት ኑሮዬን ጀመርኩኝ

ይኼኔ ነው ታዲያ በትሬን የቆረጥኳት
እኔም ልመረኮዝ በግም ልመራባት
አዲሱ ሥራዬ በጣም ተስማምቶኛል
አያስችግሩኝም በጐች ለምደውኛል

ያው እንደልማዴ በአንድ አዘቦት ቀን
ወደ ምድረ በዳ ስመራ በጐቼን
በእሳት የማይቃጠል ቁጥቋጦ አይቼ
በጎች እንዳይቀርቡት አርቄ ነድቼ
ጠጋ ጠጋ አልኩኝ ለማየት ጓጉቼ
ያችን በትሬን ብቻ በትከሻ አንግቼ

እየቀረብኩ ስሄድ ድንገት ስሜን ጠርቶ
ከቁጥቋጦው መቅረብ እንዳላስብ ከቶ
እዚያው ጋር ቁም አለኝ ጫማ አስወለቀኝ
የቆምክበት ስፍራ ቅዱስ ነውም አለኝ
ምን አለህ በእጅህ እያለም ጠየቀኝ
እኔስ ካለ በትሬ ሌላም ነገር የለኝ

ለካ የጠየቀኝ በእጄ ያለችውን
ሊጠቀም ፈልጎ እርሱ ያሰበውን
ታምር መስሪያ አድርጓት አየሁት ጌታዬን

ዛሬስ በዚህ ዘመን ጌታ ቢፈልግህ፥ ጌታ ቢፈልግሽ
ምን አለህ በእጅህ ምን አለሽ በልብሽ?
ትንሽ ትንሽ ቃሉን ቤትህ ታጠናለህ?
ፊቱንስ ፍለጋ ትንበረከካለህ?
እህቴስ ጸጋሽን ምን አድርገሽዋል?
ጌታ እየጠበቀሽ መሆኑን አውቀሻል?
ቁርጡን ልንገራችሁ
ተነሱ ባላችሁ
ሙሴ ኮልታፋ ነው በትሩም እንጨት
ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲሆኑ ምክንያት
ፈልጎ አድርጓል ታምር ለመስራት
በእናንተ እጅ ያለ አይጠቅምም የምትሉት
ብቻ ይሄ አለኝ ብላችሁ አሳዩት
ታምር ሊሰራበት እኮ ማን አግዶት!

*በሐና አበበ*

## መልካሙ እረኛዬ

መልካሙ እረኛዬ
ኢየሱስ ጌታዬ

ስለ እኔ ህይወትህን ሰጥተህ
አዳንኸኝ በመስቀል ሞተህ
ታደግከኝ ከቶ እንዳልጠፋ
ሆንክልኝ የነፍሴ ተስፋ
ሳገኝህ ስጋቴ ጠፋ

መልካሙ እረኛዬ
ኢየሱስ ጌታዬ

አንተነህ የነፍሴ ጠባቂ
ያስጣልከኝ ካውሬ ነጣቂ
ከጥፋት ጐዳና እየመለስከኝ
ከፊቴ ቀድመህ እየመራህኝ
ማምለጫ ጋሻ ሆንክልኝ

መልካሙ እረኛዬ
ኢየሱስ ጌታዬ

በቀናው መንገድ የምትመራኝ
ሁሌ ድምጽህን የምታሰማኝ
ነፍሴን ከጭንቀት አሳርፈሃል
ይኸው ሰላምህ በልቤ ሞልቷል
ይህንን ፍቅርህን እናገራለሁ
በመንፈስ ፍሬ እመላለሳለሁ
አዳኝነትህን እመሰክራለሁ
ዝም ለማለት መቼ እችላለሁ

መልካሙ እረኝዬ
ኢየሱስ ጌታዬ

*በየውብዳር ፍሰሐ*


የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን

ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON

88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org